የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት
ልሣነ- ሕግ ጋዜጣ
LISAN HIG GAZETA
OF THE BENISHANGUL — GUMUZ REGIONAL STATE

17 ኛ ዓመት ቁጥር 105
ጉባ/ማንኩሽ/ ሐምሌ 2004

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት
ም/ቤት ጠባቂነት የወጣ


## አዋጅ ቁጥር 105/ 2004

## የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የክልሉ መዝሙር አዋጅ

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ሕገ መንግስት አንቀጽ 5 መሠረት የክልሉ መንግስት የራሱ የሆነ ክልላዊ መዝሙር እንደሚኖረውና ይህም በህግ እንደሚወሰን የተደነገገ በመሆኑ፣

ይህ መዝሙር የክልሉን ህዝቦች፣ ታሪክ፣ባህል፣ እኩልነትና አብሮ ለመኖር ያላቸው እምነት እንዲሁም የወደፊት የጋራ እድላቸውን በሚያንፀባርቅ መልክ መቅረጽ በማስፈለጉ፣

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ሕገ መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### አንቀጽ 1 አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት መዝሙር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 105 / 2004 "ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 2 የመዝሙሩ ይዘት

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት መዝሙር የሚከተሉትን የሚያፀባርቅ ነው፡፡

1. የክልሉን ህዝብ የረጅም ዘመን ታሪክ፣ ባህል፣ ቅርስንና የተፈጥሮ ፀጋን፣
2. የክልሉን ህዝቦች የረጅም ዘመን የጀግንነት ታሪክ፣
3. የክልሉ ሕዝቦች በእኩልነት፣ በመግባባትና በመፈቃቀድ እንዲሁም በዘላቂ አንድነትን የሚመሠረቱበትን፣
4. ሕዝቡ ለተሻለ ኑሮ ያለው ምኞች፣

### አንቀጽ 3 የክልሉ መዝሙር ግጥምና የሙዚቃ ኖታ

1. የመዝሙሩ ግጥም እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

አዝማች

ውብ የባህል አምባ ድንግል ለምለም ምድር
የሠላም ተምሳሌት የተጋድሎ ምስጢር

ቤኒሻንጉል-ጉሙዝ እናት ክልላችን
የኛነታችን ውል መፍለቂያ ምንጫችን

በልዩነት ህብር አንድነትሽ ደምቆ
ወግ ባህል ልማድሽ በኛ ተጠብቆ
ሠላም ዴሞክራሲ ፍትህ ባንች ሰፍኖ
ዝናሽ ከፍ ብሎ ስምሽ ባገር ገንኖ

ልንጓዝ ባንድነት በልማት ጐዳና
ቃል ገባን ልጆችሽ ዳግም እንደገና፡፡

2. የመዝሙሩ የሙዚቃ ኖታ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 4 የክልሉ መዝሙር**

1. የክልሉ መዝሙር በሚከተሉት ሥፍራዎችና መሥሪያ ቤቶች ይዘመራል፡፡
ሀ. ተጠሪነታቸው ለክልሉ መንግስት በሆኑ ከተሞች /ገጠር/ ውስጥ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ሰንደቅ ዓላማን በሚያወጡበትና በሚያወርዱበት ጊዜ፣
ለ. የክልሉ ፖሊስ ሠራዊት የሰንደቅ ዓላማን በሚያወጡበትና በሚያወርዱበት ጊዜ፣
ሐ. በክልል ደረጃ በሚካሄዱ በማንኛውም የክብረ በዓላት፣ የስብሰባ፣ ስፖርታዊ ውድድሮችና ይህን መሰል ዝግጅቶች መዝጊያ ላይ፣
መ. በክልሉ ደረጃ አገልግሎት እየሰጡ በሚገኙ ማንኛውም የብዙሃን መገናኛ ድርጅቶች የየእለት ስርጭታቸው መዝጊያ ላይ፣
2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ (1) ስር በተዘረዘረው መሠረት የክልሉ መዝሙር በተገቢው ጊዜና ሥፍራ እንዲዘመር የየመሥሪያ ቤቶቹ የበላይ ኃላፊዎች የማስተማርና የማስተባበር ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

**አንቀጽ 5 የተከለከሉ ተግባራት**

1. ማንኛውም የክልሉ ኗሪ የክልሉ መዝሙር በሚዘመርበት ወቅት በተለይም ከላይ በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል ሀ-ሐ በተመለከተው ሥፍራ ላይ በሚገኝበት ጊዜ መዝሙሩ እስኪያበቃ

ድረስ ተገቢውን ክብር መስጠት አለበት፣

2. በማንኛውም ሁኔታ የሚገለጽ የመደፈር፣ የማሰናከል፣ የማወክ ወይም ሌላ መሰል ተግባራትን መፈጸም የተከለከለ ነው፣

3. መዝሙሩን የማዘመር ኃላፊነት ያለበት ሰው ወይም መሥሪያ ቤት መዝሙሩ በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች የሚያዘመር ከሆነም በመሣሪያዎች የሚተላለፈው ድምጽ በሚገባ የሚሰማ መሆን አለበት፣

4. በተበላሹ መሣሪያዎች ማዘመር የተከለከለ ነው፣

5. የመዝሙሩን ግጥምና ኖታን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 በተመለከተው ውጭ በማሻሻል፣ በመቀየር፣ በመለወጥ ወይም በሌላ በማንኛውም ሁኔታ ማዘመርም ሆነ መዘመር እንዲሁም የመዝሙሩን ግጥምና ኖታ አወራረድን ቀደም ተከተል ሳይጠብቅ ማዘመርም ሆነ መዘመር የተከለከለ ነው።

**አንቀጽ 6 ስለ ቅጣት**

ማንኛውም ሰው ይህን አዋጅ ጥሶ ሲገኝ አግባብ ባለው የወንጀል ህግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል።

**አንቀጽ 7 አዋጁን ስለማሻሻል**

ይህ አዋጅ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ ሊሻሻል ይችላል።

**አንቀጽ 8 አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ጸድቆ በልሳነ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አሶሳ

ጥር 30/2004 ዓ/ም

አህመድ ናስር አህመድ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት

ፕሬዚዳንት